# <u>ለመሪው የተዘጋጀ</u>

## <u>ጥናት አንድ (ይሁዳ ቁጥር 1-7)</u>

1. ይሁዳ በመጀመሪያ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ እንደሆነ ሲነግረን በሌላ በኩል ደግሞ የያዕቆብ ወንድም እንደሆነም ይነግረናል፡፡ የኢየሱስ ወንድም ሆኖ ሳለ ባርያነቱን ብቻ መንገሩና በራሱ በጥንቷ ቤ/ክ ታዋቂነት ስላልነበረው የያቆብን ስም ራሱን ለማስተዋወቂያ መጠቀሙ እነዚህ ሁለት ነገሮች ተጣምረው የጸሐፊውን ትህትና ያመለክቱናል፡፡
2. እውነተኛ አማኝ በእግዚአብሄር የተጠራ ነው፤ በአብ የተወደደ ሲሆን በመጨረሻ ደግሞ በክርስቶስ የሚጠበቅ ነው፡፡
3. ይህንን በሃሰተኛ አስተማሪዎች ላይ ያተኮረ መልዕክት ከመጻፉ በፊት ሊጽፍ የነበረው ደህንነታችንን በተመለከተ ነበረ፡፡ ይህንን ርዕስ የመረጠው የተሸለ ስለሆነ ሳይሆን ሃሰተኛ አስተማሪዎቹ ቤ/ክርስትያን ውስጥ የገቡ ስለሆነ አንገብጋቢና ጊዜ የማይሰጥ ስለሆነ ነው፡፡
4. ጸሃፊው በመጀመሪያ ያሰበውን ርዕስ ቢጽፍ በክርስቶስ ስላገኘነው ደህንነት ለእግዚአብሄር ምስጋናን በማቅረብ መጀመሩ አይቀሬ ነው፡፡ የይሁዳ ስም ትረጉምም «ምስጋና» ነው፡፡
5. ከረጅም ጊዜ በፊት ለፍርድ የተጻፉ ናቸው  
   ፈሪሃ እግዚአብሄር የላቸውም  
   ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው  
   የሚገቡት ሾልከው ነው  
   ጸጋውን በርኩሰት የሚለውጡ ናቸው
6. በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎች ያለፈውን መርሳት የተለመደ ስለሆነና በሌላ በኩል ደግሞ የሚያውቁትን ታሪክ በተግባር በሌሎች ህይወት ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደሚችል ለማስተማር ነው፡፡
7. ሀ) ከግብጽ ወጥተው ባለማመን ምክንያት የጠፉትን  
   ለ) ቦታቸውን ያላወቁትና ፍርድ ስለሚጠብቃቸው መላዕክት  
   ሐ) ለሴሰኛነትና ለርኩሰት ራሳቸውን በመስጠታቸው ስለተፈረደባቸው ከተሞች፡፡  
   ለእነዚህ ሁሉ የጋራ ሆኖ የምናየው ዋነኛ ነገር «የእግዚአብሄር ፍርድ» የሚለውን ሃሳብ ሲሆን እነዚህ ሃሰተኛ አስተማሪዎችም «ከእግዚአብሄር ፍርድ» እንደማያመልጡ ለመናገር ነው፡፡
8. እያንዳንዱ የራሱ የሆነ መልስ በመስጠት ተወያዩበት፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት ሁለት (ይሁዳ ቁጥር 8-16)

1. «ህልም አላሚዎች» ሲል ምናልባት የሀሰት ትምህርታቸውን ለማሰራጨት የሚጠቀሙት ትምህርቱን በህልሜ ተናገረኝ ብለው ያቀርቡ ይሆናል፤ ወይም ደግሞ ቅዠታምነታቸውንም ለመናገር ሊሆን ይችላል::
2. የገዛ ስጋቸውን ያረክሳሉ፤ ሥልጣንን ይቃወማሉ፤ በሰማይ ክብር ያላቸውንም ፍጥረታት ይሳደባሉ:: ስለ ሚካኤል በመናገር ሊያስጠነቅቀን የፈለገው ነገር መናፍስትን የመሳደብ መብትና ስልጣን እንደሌለን ለማስተማር ነው::
3. በዚህች አጭር መልዕክት ውስጥ በብዛት የብሉይ ኪዳን ነገሮችን መጥቀሱ አይሁዶችን ያተኮረ መሆኑ ይታያል::
4. በቃየን መንገድ ስለሄዱ(ዘፍ 4)፤ በበለዓም ስህተት ውስጥ ስለወደቁና(ዘኁ 22-23) በቆሬ ዓመጽ ስለጠፉ (ዘኁ 16):: የቃየን መንገድ በመስዋዕት ሳይሆን በጉልበቱ ያፈራውነ (በጥረት) ወደ እግዚአብሄር ለመቅረብ የሚደረግ ሙከራ፤ የበለዓም ስህተት ከእግዚአብሄር ፈቃድ ይልቅ ለገንዘብ መገዛትና የቆሬ ዓመጽ ደግሞ ትዕቢትና ንቀት ናቸው::
5. እነዚህን ሰዎች የሚመስላቸው ሀ) ራሱን በሚመግብ እረኛ ለ)ዝናብ የሌለው ደመና ሐ) በመከር ወር ዝናብ እንደማይገኝበት ዛፍ መ) የተቆጣ የባህር ማዕበል ሠ) ተንከራታች ኮከብ
6. ይሁዳ ይህንን ለማለት የደፈረበት ምክንያት በቁ 4 ላይ በሰፈረው ሃሳብ ላይ ተመስርቶ ነው:: እኛም የዚህ አይነት ሰዎችን በድፍረት ለመናገር እንችላለን::
7. እነዚህ ሰዎች አጉረምራሚዎች ናቸው፤ ሌሎችን የሚከሱ ናቸው፤ ርኩስ ምኞታቸውን ይከተላሉ፤ በራሳቸው ይታበያሉ፤ ለጥቅም ሲሉ ሌሎችን ይክባሉ:: ከዚህ የምንማረው ሃሰተኛ አስተማሪዎች ትምህርታቸው ብቻ ሳይሆን አኗኗራቸውም ሊያጠራጥረን እንደሚገባ ነው::
8. የጥናቱ ተከፋዮች የየራሳቸውን አመለከከት በመናገር ሃሳብ እንዲለዋወጡ አበረታታቸው/ቻቸው::

# ለመሪው የተዘጋጀ
# ጥናት ሶስት (ይሁዳ ቁጥር 17-25)

1. የተናገረው ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲሆን የተናገረውም በ2ኛ ጴጥ 2:1 እና 3:3 ላይ ይነበባል::
2. ዋርያቱ ስለነዚህ ሰዎች ተናገሩ የሚለው ዋና ነገር «ርኩስ ምኞታቸውን የሚከተሉ ዘባቾች» እንደሚመጡ ነው:: ርኩስ ምኞት የሚከተሉ ማለት: ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሄር ቃል የሚናገራቸውን ሳይሆን የራሳቸውን ምኞት ማድረግ የሚፈልጉ ማለት ነው:: የሰው ምኞት ደግሞ በእግዚአብሄር መንፈስና ቃል ከልተገራ ርኩሰት አያጣውም::
3. መለያየትን የሚፈጥሩ፤በደመ ነፍስ የሚሄዱ፤ መንፈስ የሌላቸው ናቸው::
4. እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሄር የተጠሩ፤ የተወደዱና በኢየሱሰ ክርስቶስ የተጠበቁ ናቸው(ቁ1) እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን ገዣቸውና ጌታቸው መሆኑን የተቀበሉ ሰዎች ናቸው(ቁ4) አነዚህ ሰዎች የፍቅር ግብዣ የሚገባበዙ ናቸው(ቁ12)::
5. ለእውነተኛ አማኞች ይሁዳ የሚመክራቸው: እጅግ ቅዱስ በሆነው እምነታቸው ራሳቸውን እንዲያንጹ፤ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጸልዩና፤ በእግዚአብሄር ፍቅር ራሳቸውን እንዲጠብቁ ነው:: በእግዚአብሄር ፍቅር ራስን መጠበቅ ማለት በህይወታችን የሆነውና እየሆነ ያለው ወደፊትም የሚሆነው ማናቸውም ነገር ክእግዚአብሄር ፍቅር የተነሳ እንደሆነና በጊዜው በጎ የማይመስለን ነገር እንክዋን በእርሱ ፍቅር ለበጎ እንደሚሰራልን በመተማመን መመላለስ ማለት ሊሆን ይችላል::
6. ሀ) ተጠራጣሪዎቸ (ርህራሄ ማሳየት)፤ ለ)በእሳት ውስጥ የገቡ/በትምህርታቸው የተወሰዱና(ነጥቆ ማውጣት) ሐ) ሌሎች (ምህረት ማድረግ:: እነዚህን ሁሉ ሲያደርጉ አማኞቹ በጣም በጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸውም ይነግራቸዋል::
7. እንዳንወድቅ ይጠብቀናል፤ ያለነቀፋ ያቀርበናል፤ በደስታ ይጠብቀናል:: በቁ1 እና 24 ከሰፈሩት ሃሳቦች አማኝ ላለመውደቅ በሚያደርገው ጥረት ሳይሆን እንዳይወድቅ የሚጠብቀው ራሱ እግዚአብሄር እንደሆነ ያሳየናል::
8. እያንዳንዱ የራሱን መልስ ይስጥና ተወያዩበት::